# ሞት ሲዘገይ የቀረ ይመስላል

ይሄይስ አእምሮ

የኢትዮጵያም ሆነ የሌላው ዓለም ሁኔታ ሁሉ ግራ እሚያጋባ ሆነና ምን ብዬ እንደምጀምር ግራ ገባኝ፡፡

ሰዎች በባሕርያችን ተስፋ አስቆራጭ ፍጡራን ነን፡፡ በተለይ የአሁኑ ዘመን አብዛኛዎቹ ሰዎችማ ከምን ጊዜውም በበለጠ የክፉ ክፉ እዬሆንን በመምጣታችን እንዲያውም በአረመኔነቱ ከለየለት መጥፎ አውሬ እየባስን መጥተናል ማለት ይቻላል፡፡ ግን ምን ቢነካን ይሆን? ለምንድን ነው ይህን ያህል ለገንዘብና ለሥልጣን አቅላችንን ስተን ሁሉንም የኅሊናና የሃይማኖት አጥሮች ጥሰን ባለ በሌለ ኃይላችን ለሁለንተናዊ ኪሣራ በገዛ ፈቃዳችን የምንጋለጠው? ሰውነታችንን ምን ዓይነት ኢጋንንት ቢኮናተሩት ይሆን እስከዚህ የሞራልና የጤናማ ሰው ምልክቶችን ሙሉ በሙሉ ማለት በሚቻል ሁኔታ ደምስሰን ለግልና ለቡድን ጥቅም የምንሸነፈው?

እነዚህ ሥልጣንና ገንዘብ ሰውን የሚያሳውር አንዳች ምትሃታዊ ኃይል አላቸው፡፡ ሰው ገንዘብና ሥልጣን ለማግኘት የማይፈነቅለው ድንጋይ እንዳይኖረው የሆነበት ምክንያት ምንጩ ሰይጣናዊ መሆኑ የምንክደው አይመስለኝም፡፡ ሰይጣን ደግሞ አደገኛ መርዝ ነው፡፡ ሰውን ከሰው ያባላል፤ ያጨራርሳል፡፡ ከሰማይ በታች ከምድር በላይ የማይጠቀመው ዘዴ ወይም ሥልት የለም - የማፋጀት ዓላማውን ለማሣካት፡፡ ዘረኝነት፣ ጎሠኝነት፣ቋንቋ፣ የመንደር ልጅነት፣ ሃይማኖት... ዋና ዋናዎቹ የማጨራረሻ መንገዶቹ መሆናቸውን ከኛዋ ምሥኪን ሀገር እውነተኛ የወቅቱ ገጠመኝ ተነስተን የምንረዳው ነው፡፡ ሰይጣን ዓላማው ይሣካለት እንጂ ባህልና ይሉኝታ ብሎ ነገር አያውቅም፡፡ ቄስና ጳጳስ፣ ዲያቆንና መዘምር፣ ነጋዴና ፖለቲከኛ ብሎ ነገርም አያውቅም፡፡ ዓላማውን ያሣኩለት እንጂ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል በተለይ ቁንጮ አካባቢ ያሉት የርሱ አጫፋሪዎችና ባለሟሎቹ ናቸው፡፡ ለዚህ ሀገራችን ዋና ምሣሌ ናት፡፡ በተለይ በአሁኑ ወቅት ሰይጣን እንደልቡ የማይጨፍርበት የአምልኮት ቤትና የባለሥልጣን ቢሮ በሀገራችን የትም ቦታ አይገኝም፤ ከሞላ ጎደል ሁሉም የርሱ አጋፋሪ ሆኗል፡፡ ሁላችንም በእርሱ ግዛት ሥር ወድቀናል ማለት ይቻላል፡፡ ባይሆንማ ኖሮ ቅድስት ሀገራችን በሁሉም መለኪያ የሁሉም ሀገሮች ውራ አትሆንም ነበር፡፡ ...

የሦሪያው አሠድ እሳት(ባሽር አል አሣድ) ሕዝብን በእቶን እሳት መለብለብ ከጀመረ ዓመት ሊሞላው ነው ወይም ሞልቷል፡፡  በየቀኑ እንደቅጠል የሚረግፈው የሕዝብ ሕይወት ለሥልጣኑ አንድ ቀንም ቢሆን ውሎ ማደር እስከጠቀመ ድረስ ደንታው አይደለም - ትልቅ መረገም፤ ለሕዝቡም ለራሱ ለሰውዬውም ለሀገሪቱም፤ ለዓለም ሕዝብ በጠቅላላውም የሀፍረት ምንጭ ነው፡፡ የሌሎች ዓለማት ፍጡራን (ካሉ) በሰዎች አውሬያዊ ባሕርይ እንዲሳቀቁ የሚያደርግ አንዱ ማፈሪያ ልጃችን አሣድ ነው - እርግጥ ነው ከመለስ ዜናዊ ቀጥሎ ፤ ይሠመርበት - ከመለስ ዜናዊ ቀጥሎ፡፡ እንደመለስ ጨካኝና መሠሪ በዓለም የለም፡፡ ይህን ለማረጋገጥ የኢቲቪን የላም አለኝ በሰማይ ተረት ተረት ሣይሆን እውነተኛውን የሕዝብ ኑሮ እዚህ ሀገር ውስጥ መጥቶ መመልከት ነው፡፡ በወያኔ ጨንገር የማይሸነቆጥ ከወያኔ ከራሱ በስተቀር ማንም የለም፡፡ አሁንማ ብሎ ብሎ ሕዝቡ አንዳችም የሚመካበትና ሸጦ ለውጦም የልጆቹን ጉሮሮ የሚዘጋበትን የመጨረሻ አማራጩን ቤቱን እንኳን እንዳያዝዝበት ‹ያንተ አይደለም› ብሎታል፡፡ ይህ ሕግ የአልባኒያ ይሁን የታላቋ ብሪጣንያ ገና አላወቅነውም፡፡ ወያኔ በጉብዝናው እንደቀጠለ ነው፡፡ በአባይ ሰበብም ሕዝቡን በጊንጣዊ ጅራፍ መግረፋንም እንደቀጠለ ነው፡፡ አዲስ አበባ ውስጥ ድሃን አልይ ብሎ የጥቂቶች ከተማ ለማድረግ ቀን ከሌት ደፋ ቀና ማለቱንም እንደቀጠለ ነው፡፡ በቃላት መግለጽ በሚከብድ የኑሮ ውድነት ጅራፍ ወያኔ ያልሆነን የሕዝብ ክፍል መቀጥቀጡንም እንደቀጠለ ነው፡፡ ወያኔ ጀግናው እንደጆን ወከር - እንደ ‹ዮሐንስ ተራማጁ› በ‹still going strong› መርሁ መራመዱን እንደቀጠለ ነው፡፡ ያልተመለሰና ለመመለስ ያስቸገረን ጥያቄ ግን ‹ እስከማዕዜኑ?› - እስከመቼ - የሚለው ጥያቄ ነው - ለጊዜው፡፡

ሰው የሚመስሉ በሰው አምሳል እንደምንም ቤተ መንግሥት ገብተው ሲያበቁ የሰውነት መገለጫ ማስመሰያ ለምዳቸውን አውልቀው የአውሬነት ባሕርያቸውን የሚላበሱና ሀፍረትና ይሉኝታን ቸብችበው ሸጠው የበሉ ሥልጣንን ሙጭጭ ብለው የቀሩ የኢጋንንት ውላጆችን ብዛት የዓለም ሀገሮች አብያተ መንግሥት ይቁጠሩት፡፡ እያንዳንዳቸውን ከነጉድፋቸው እንዘርዝር ብንል ውለን እናድራለን፡፡ የሰሞኑን የሴኔጋሉን ሰውዬ እንኳን ብናይ ከማንምና ከምንም ሊማር ያልቻለ ደደብና የገልቱ ገልቱ መሆኑን እንገነዘባለን - የዚያኛውን ሰሞን የኮት ዲቯሩን የሎራን ባግቦን ቅሌት ሳንዘነጋ፡፡ ሕገ መንግሥቱ አንድ ሰው ከሁለት ዙር በላይ ለመሪነት መወዳደር አይችልም ብሎ የደነገገውን ልክ እንደቬንዝዌላው አምባገነን ሁጎ ሻቬዝ በቀጭን ትዕዛዝ በፍርድ ቤት አስለውጦ ለሦስተኛ ጊዜ እንዲወዳደር የሚያስችል አዲስ ሕግ በሕገ መንግሥቱ እንዲሰነቀር በማድረጉ አመጽ እየተቀሰቀሰ ነው፡፡ በውነት ግን ሰዎች ምን ነካን?

የኛው ጉድ መለስም ዓለምን ለማጭበርበር እየሞከረ የቤን አሊን የሥልጣን ዕድሜ ሊደርስ የቀረው ጊዜ ጥቂት ነው፡፡ ዓለም የአጭበርባሪዎች ናት፡፡ ዓለም የሌቦች ናት፡፡ መልካም ሰዎች በዚህች ዓለም ሥፍራ የላቸውም፤ ካላቸውም ያ ጊዜ አልፏል ወይም ገና አልመጣም፡፡ የጋናው ጸሐፊ አይ ኪው አርማህ ‹ቆንጆዎቹ ገና አልተወለዱም› እንዳለው ነው ነገሩ በጅምላው ፡፡ ...

ኢትዮጵያ ውስጥ አራት ኪሎ ላይ የተገሸረው የወያኔ መንጋ በሕዝብ ላይ እንደተጸዳዳ ይሄውና ሃያ አንድ ዓመታትን ሊያስቆጥር የቀሩት በአንድ ዕጅ ጣቶች የሚቆጠሩ ጥቂት ወራት ብቻ ናቸው፡፡ ይህን የወሮበሎች የጥፋት መንጋ ከአራት ኪሎ ለማስወጣት እስካሁን ዝምቡን እሽ ያለው የለም - ‹ነጻ አውጪው› ሁሉ እርስ በርሱ ይፈሳፈስ ወይንስ የጋራ ጠላትን ለማ‘ቸ’ነፍ በኅብረት ይቁም፤ ጉድ እኮ ነው ‹በሬው ሳይገዛ ሌባው በረት ሞላ›አሉ? በርግጥ ግን ምን ነካን? ወዴትስ እያመራን ይሆን? የመማሪያ የሰውነት ክፍላችን ጭራሹን ሥራ አቆመ ይሆን? ተስፋ የቆረጠው ወገን በ‹ሀገር ሲወረር አብረህ ውረር› የቆዩ የሆዳሞች መመሪያ መሠረት ከወያኔ ጋር እየተሻረከ በፖለቲካው፣ በሃይማኖቱና በንግዱ ዘርፍ ሕዝቡንና ሀገሪቱን መቦጥቦጡን ቀጥሏል፡፡ በዚያም ሳቢያ በሀብታሙና በድሃው መካከል ያለውን ርቀት ለመሥፈር ዓለም ከደረሰችበት የልኬት መጠን ማወቂያ መሣሪያ አቅም በላይ ሆኖአል፡፡ በአዲስ አበባ በሚሊዮን የሚገመት ድሃ በጥቂት ሺዎች ከሚቆጠሩ የናጠጡ ሀብታሞች ቤት የሚጣለውን ቆሻሻ - ከሰውነት ተራ ወርዶ -  አንዳች የሚቀመስ ፍርፋሪ ወይም የሙዝ ልጣጭ ለማግኘት በየቆሻሻ ገንዳው እንደዝንብ ሲርመሰመስ ስታዩ ኢትዮጵያዊነት ላይ የወረደው መቅሰፍት ያስለቅሳችኋል - የርህራሄ መንፈሳችሁ እንደሀብታሞቻችን ተሟጦ ካላለቀ፡፡ ሀብታሙ አእምሮውን አጥቷል፤ ድህነቱም ቅጥ አጥቷል፡፡ የምፅዓት ጊዜ የተቃረበ ይመስላል...፡፡ ለማንኛውም ግመሊቱ እየተጓዘች ነው፤ ውሾቹም እየተከተሉ ናቸው፡፡

አሁንም ‹እስከመቼ?› ለሚለው ጥያቄ መልሱን ጊዜ ባለውሉ እስኪሰጥ ድረስ መጠበቅ ብቻ ነው፡፡ አንድ እውነት ግን አለ፤ ያም እውነት ሁሉም የከፋት ስንቅ የሚያልቅ መሆኑ ነው፡፡ እናም ወያኔዎች ያማረባቸው ወቅት እንደነበረና እንዳለም ሁሉ እንደቢጤዎቻቸው እንደነጋዳፊና እንደነሂትለር መቃብሩ ተቆፍሮ እንደሚጠባበቀው እንደአሣድም ጀምበር ስትጠልቅባቸው የሚሆኑትን መሆን ዕድሜ የሰጠው የሚያየው ይሆናል፡፡ ይህን እውነት ለመናገር ነቢይነትን አይጠይቅም፡፡ የታሪክን አካሄድ ብቻ ማጤን ይበቃል፡፡ ብሂሉ ‹ከተራበ ለጠገበ አዝናለሁ› እንዲል የምናሳዝን እኛ ድሆችና ምንዱባን ሳንሆን ያደርጉትን አጥተው በገዛ ሀገራችን የተዋራጅ ተዋራጅ ያደረጉን ጥጋበኞቹ ናቸው፡፡ እኛማ …

እሳት ላይ የተጣደን ውኃ ወይም ወተት በምናባችሁ አስቡ፡፡ በቅድሚያ ለስ ይላል፤ ሂደቱ ይቀጥላል - ይሞቃል፤ ይፍለቀለቃል፤ ይንተከተካል፤ በመጨረሻም ይገነፍላል - በዚህ ሂደት የሚተንም አለ - እሚገባበት እማይታወቅ፡፡ የገነፈለን ወተት ደግሞ ማቆም የሚቻለው አንድም ኃይል የለም፡፡ እርግጥ ነው ያቺን ወተቱ የሚፍለቀለቅባትን ወይም የሚገነፍልባትን ቅጽበት ለይቶ ማወቅ ይገባል፤ ግን እሱም ከባድ ነው - ማወቅ ያስቸግራል፡፡ ከዓለም የማኅበራዊ ሣይንስ ሊቃውንት መካከል አንዷት ምሁር ባደረጉት አንድ ቀደም ያለ ጥናት መሠረት በአንድ ሀገር ሕዝባዊ አመጽ ሊያስነሱና ያለውን መንግሥት ሊጥሉ የሚችሉ ቅድመ ሁኔታዎች በሀገራችን ከተሟሉ በጥቂቱ 30 ዓመታት አልፈዋል፡፡ ይህ ኢትዮጵያ ላይ ሲደርስ ከተጠቀሰው ጥናት ያፈነገጠ ሁኔታ አንዳንዶቻችንን ሊያስደነግጥ ሊያስበረግግም ቢችል አይገርምም፡፡ ያም ሁኔታ ለገዢዎች የልብ ልብ እየሰጠ ይበልጥ እንዲጋልቡን በር መክፈቱን ብንጠራጠር አይፈረድብንም፡፡ እውነቱ ግን በባህላዊው አገላለጽ ‹በቅሎ ገመዷን በጠሰች› ቢባል ‹ ማሠሪያዋን አሣጠረች› እንዲሉ ዓይነት ነው፡፡

የሦሪያና የሊቢያ ሕዝብ ከዐርባ ዓመታት በኋላ ከእንቅልፉ ነቅቶ ምን እንደሠራ የምንታዘብ ወገኖች ወያኔ ይዋል ይደር እንጂ በሦፈረው ቁና ዕጥፍ ድርብ እንደሚሠፈረው ቅንጣት መጠራጠር አይገባም፡፡ የገዢዎች የአገዛዝ ሥልት በጣም ተለዋዋጭና ከዓለም ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እየተገነዛበ እዩዘመነ የሚሄድም ነው፡፡ ገዢዎች በመሠረቱ የማይጠቀሙት ዘዴ የለም፤ ኮከብ ቆጣሪና መጣፍ ገላጭም ጭምር ሊጠቀሙ ይችላሉ - የፖለቲካ አሰለጦቻቸው ከሚሰጧቸው ሸር የተሞላበት የምክር አገልግሎት በተጨማሪ፡፡ ይሁንና ትብታብም በሉት አፍዝ አደንግዝ ወይም የሸረኞች ምክር የሚሠራበትና የማይሠራበት አቡሻክርና አበቅቴ አለ፡፡ ሁል ጊዜ ፋሲካ የለም፡፡ እነሱ ይህን እውነት ቢጠራጠሩ ወይም ለማመን ባይፈልጉ ሞራና ስብ አንጎላቸውን ስለደፈነው ሊሆን ይችላልና አይደንቅም፤ የሥልጣንና የገንዘብ ሱስ ዐይንን ይጋርዳል፤ የኅሊናን ጓዳ ያጨልማል፤ ማሰቢያ አካልን ከነአካቴው ከሥራ ውጪ ያደርጋል፡፡ ይህ ደግሞ በወያኔ ብቻ የተወሰነ ሣይሆን ሊወድቅ አንድ ሐሙስ በቀረው በሦርያው የሕዳጣኑ ነገድ ተወካይ በአሣድም እያስተዋልነው ነው፡፡

‹መብሰሉ ላይቀር ጭንቅላት ብዙ እሳት ይፈጃል› ይባላል፡፡ ሌላም አለ፤‹ ይዋል ይደር እንጂ አህያ የጅብ ናት› የሚል፡፡ ከዚህ ነባራዊ እውነታ አንድም ሰው አንድም መንግሥት አንድም ምድራዊ ተቋም ነጻ ሊሆን አይቻለውም፡፡ የሥራን ማግኘት ከፍትህ አምላክ ከፈጣሪ የሚላክ እንጂ እኔና አንተ በፈቃዳችን የምናስገኘው ሰብአዊ ስጦታ ወይም ችሮታ አይደለም፡፡ ወያኔ አሁን ሊፈነጥዝ ይችላል፤ ለቀጣቹ ሃያና ሠላሣ ዓመታትም እንዲሁ ጮቤ እየረገጠ ሀገርንና ሕዝብን እንዳሁኑ በሲያላዊ ጨካኝ አገዛዝ አፍኖ ሊያሰቃይ ይችላል፡፡ የማያመልጠው የታሪክና የፈጣሪ ዕዳ ግን በልጆቹም ቢሆን የማያጣው ጨካኝ ተፈጥሮው የሚያስከፍለውን ውድ ዋጋ ነው፡፡ እንጼ - የአሣድ አባት ሀፌዝ አላሣድ እኮ አሁን በመቃብሩ ውስጥ አጥንቱ እየተገላበጠ ነው - ልጁን ለማገዝ እዩፈለገ ግን በፈጣሪ ዕጅ ተይዞ ሥጋው ትቢያ ነፍሱም የጀሃነብ ምርኮኛ ሆነውበት፡፡ ይህን መሠረታዊ ዕውቀት እኮ ነው አምባገነኖች የተነጠቁት፤ ይህን ሰው በዚች ምድር የሚያብብበት፣ የሚያፈራበት፣ የሚጀግንበት፣ የሚገንበትና የሚዋረድበት ዘመን ኢምንት መሆኑን መርሳት እኮ ነው የአምባገነኖች ትልቁ ያለማስተዋል በሽታ፡፡ ለመሆኑ አንድ ሰው ሌላውን ሰው ቢያሰቃይ ምን ይጠቀማል? የደስታው እርዝማኔና ዘላቂ ውጤቱስ ምንድነው? አንድ መቶ ዓመት እንኳን በሕይወት  ሊኖር የማይቻለው ይህ ደካማ ፍጡር - ሰው - ለቅጽበታዊ መናኛ ዕድሎች እየተንበረከከ በወገኖቹ ላይ መከራና ሰቆቃ የሚያዘንበው ምን ሊጠቀም ይሆን? ሰውን ምን ነካው? እንዴት ከቀሪው የእንስሳት ዓለም ይነስ? እርግቦች በእርግብነታቸው፣ ከብቶች በከብትነታቸው፣ ድመቶች በድመትነታቸው… ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ ሲቀራረቡ እኛ ሰው የመሆናችን የጋራ ተፈጥሮ ሳያንሰን እንዴት በግንባር ላይ ምልክቶችና በልሣናዊ የመግባቢያ መሣሪያ ላይ ተመርኩዘን አንዱን እናቀርባለን ሌላውን እናርቃለን? ይሁን፤ ማቅረብ ማራቁ ግዴለም፡፡ ከሰውነት ተራ በወረደ መጥፎ ጠባይ ተለክፈን ዘራችን የምንለውን ልዩ ሥልጣንና ጥቅም እንዲያገኝ ስናደርግ ሌላውንና የጥቅማችን ተቀናቃኝ ነው ብለን የፈረጅነውን ሰው ሰበብ አስባብ እዩፈለግን ከሥራውና ከኑሮው የምናፈናቅለው፣ ሰላማዊ ኑሮውን የምናዛንፈው ለእሥርና ለእንግልት ለስደትና ለሞት ለድህነትና ለባርነት ኑሮ የምናጋልጠው ለምንድነው? ለዚህ ወንጀላችንስ ሰው ዋጋችንን ባይሰጠን ለይምሰል በሰው ፊት ስሙን የምናነሳውና የውሻን ደም ሳይቀር በከንቱ የማያስቀረው ፈጣሪስ ዝም ብሎ ያልፈናል ወይ? ከየት የመጣብን ድንቁርና ነው? በእውኑ ሰዎች ምን ነካን? ክፉ ደስታ አንጎልን መደፍጠጥ አለበት ወይ? ኧረ ትንሽም ብትሆን ጊዜ ካለችን በዚህ ጉዳይ መጨነቅና ማሰብ የሚገባን ወገኖች ቆም ብለን እናስብበት፡፡ (ለምለው ነገር የኢትዮጵያን የፖለቲካና የሃይማኖት የሹመት አሰጣጥና የሀገሪቱን አጠቃላይ ወቅታዊ የሀብት ክፍፍል ልብ ብለው ያጤኗል፤ ዝርዝር ኪስ የቀዳል፡፡)

የወያኔ ባንክን ያስጨነቀ ገንዘብ፣ የወያኔ አዲስ አበባን ያጨናነቀ የንግድና የመኖሪያ ሕንጻ፣ የወያኔ ከድሃው ሕዝብ በየምክንያቱ የተመዘበረ ሀብትና ንብረት ለወያኔ ምን ይጠቅማል? 80 ሚሊዮን ሕዝብ በማስጨነቅና መቅኖ በማሣጣት የተገኘ ሥልጣንና ሀብት እስከመቼ ይቆያል? የጋዳፊ በቢሊዮን - ከዚያም በላይ - የሚቆጠር ዶላር በመጨረሻው መጨረሻ ላይ ገና ሳይሞት በመቀመጫው ሣንጃ ሲከቱበት ምን ረዳው? መለስና ቢጤዎቹ የዓለም ደናቁርት መሪዎች ከነዚህ በነጻ ከሚገኙ ትምህርቶች - ሣንቲም ሳይከፍሉ እንዲሁ በብላሽ -  መማር እንዴት ተሣናቸው? ምናልባት የኛ ኃጢያት መብዛት? ጠርጥሩ፤ ቆሻሻ ቆሻሻን የማጽዳት የሞራል ብቃት የለውም፡፡ ‹ብዔል ዘቡል ብዔል ዘቡልን አያወጣም› እንዲል መጽሐፉ፡፡ ስለዚህ ራሳችንንም እንፈትሽ፡፡ ሰውን ስናስጠነቅቅ ከሌባ ጣታችን በመለስ ሦስቱ ጣቶች ወደኛ መዞራቸውን ልብ እንበል፡፡ የኛ የገረረ ልቦና፣ የኛ የተበከለ አስተሳሰብ፣ የኛ የተንሸዋረረ አመለካከት፣ የኛ የቆሸሸ ስብዕና፣ የኛ ፍትህ አልባነት፣ የኛ መጥፎ ምግባር፣ የኛ ብዙ ነገር… ለወያኔ ተመቻችቶ መቀመጥ ዓይነተኛ ግብኣት ነው፡፡ እንዲያ ባይሆን ከአምሥት የማይበልጡ አጋሚዶዎች እንዲህ ባልተዘባነኑብን ነበር፡፡ ‹ትግል ከራስ› ብላለች ድምጻዊት አሥር አለቃ ውቢሻሽ በ‹ከቆራጡ መሪ…› አልበሟ- ያኔ ጥንት፡፡

ነገር ቢበዛ በአህያ አይጫንም፡፡ ጥቂት ነገር ልበልና ላብቃ፡፡ አዲስ አበባ እየተንተከተከች ናት፡፡ ትዕዛዝ እንደሚጠባበቅ ሠራዊት በተጠንቀቅ ላይ ትገኛለች፡፡ ትዕዛዙ ከፈጣሪ ነው፡፡ መጽሐፉ እንዲህ ይላል፤ ‹ ኢድኅን ንጉሥ በብዝኃ ሠራዊቱ›፡፡ አዎ፤ በዕጃችን የያዝናት ብርጭቆ

መቼም የምትሰበር አትመስለን ይሆናል፤ በሰውነታችን የያዝነው የጤንነት ፀጋ መቼም የሚከዳን አይመስለን ይሆናል፤ ያለን የሚመስለን ጥንካሬ እስከወዲያኛው የማይለየን ሊመስለን ይችላል፤ የምናምናቸው ሰዎች - አሽከሮችና ደንገጡሮች እስከዝንተዓለሙ እንደታመኑ የሚዘልቁ ሊመስለን ይችላል፡፡ ነገር ግን ጊዜ ባለውሉ ዘመም ሲል ሁሉም የእንቧይ ካብ ይሆንና ሰማይ ምድር ይደፋብናል፡፡ ያኔ ስህተትን ለማስተካከል ፍላጎቱ ቢኖረንም እንኳ ዕድሉ ላይኖረን ይችላል፡፡ ከመነሻው ማስተዋልን የተነጠቀ ሰው ደግሞ በመጨረሻው በከንቱ ቢጮህ የሚያዝንለትም ሆነ የሚደርስለት አይኖርም፡፡ ታሪክ እሚያስተምረን ይህንን ነው፡፡

ሌሎች ለሥልጣንና ለሀብት ያቆበቆብን አለን፡፡ ወጡ ሳይወጠወጥ የባሕርይ አባታችን ዲያቢሎስ ገና ምኑም ሳይያዝ በሰውነታችን ገብቶ እያቅነዘነዘን የምንገኝ ወገኖች በርካቶች ነን፡፡ ሕዝቡን ከአንዱ የመከራ ጫፍ ወደሌላ የመከራ ጫፍ ለመክተት ሌት ከቀን የምንፍጨረጨር በረትንም የምናምስ አለን - በዉጭም በሀገር ውስጥም፡፡ ከአበራሽ ጠባሣ ላለመማር ምለን የተገዘትን በየአጥቢያው ሞልተናል፡፡ ያ ዓይነቱ የደካሞችና የልቦናና የኅሊና ሥውራን ዕኩይ ተግባርም ነው ከኃጢያታችንና ብልሹ ምግባራችን ጋር ተዳምሮ የነጻነት ጊዜያችንን እያዘገየብን ያለው፡፡ እንጂ ወያኔ አንድም ኃይልና ሀገር የማስተዳደር ብቃትና ችሎታ ኖሮት እንዳልሆነ ልንረዳ ይገባል፡፡ የነጻነት ኃይላት በሚባሉ ወገኖች ሥውር ጠላቶችና ከፋፋዮች በማስረግ ዕድሜውን እንዲረዘም የምናደርግ የጠላት ሕቡዕና ግልጽ ተላላኪዎች ሞልተናል፡፡ ይህም ጊዜው ባለመድረሱ እንጂ የወያኔም ሆነ የቡችሎቹ ጥንካሬ ወይም ዘዴና ብልሃት አይሎ መገኘት አይደለም - በጭራሽ!...

በአንዲት ሰሞነኛ ቀልድ ልለይ - አንዱ ነው በቀደምለት የነገረኝ - በፌስ ቡክ የተላከልኝ ብሎ፡፡ ያልሰማችሁ ፈገግ ለማለት ሞክሩ፡፡

መለስ፣ ባለቤቱ አዜብና ልጁ ሰምሃል በአውሮፕላን ተሣፍረው እዬሄዱ ነው - ወደመቀሌ፡፡ በወሎና ሸዋ ድንበር አካባቢ ሲደርሱ መለስ ‹ የኢትዮጵያ ሕዝብ መቼም ከችግርና ከችጋር አይወጣም - አንድ መቶ ብር ቁልቁል ልወርውርና አንዱን ኢትዮጵያዊ ላስደስተው› ይላል፡፡ ሚስቱ አዜብ ቀበል ታደርግና ‹እንደሱ ካሰብክስ ለምን መቶውን ብራ ለሁለት ሰንጥቀህ አምሳ አምሳውን በመወርወር ሁለት ኢትዮጵያውያንን አታስደስትም› ትለዋለች፡፡ ልጂት ሰምሃል ደግሞ የተሻለ ነው የምትለውን ሃሳብ ‹ አባዬ፣ ያንተም የእማዬም ሃሳብ ጥሩ ነው፡፡ ነገር ግን አንድ ወይም ሁለት ሰው ከምታስደስት ለምን መቶውን ብር በአሥር ቦታ ዘርዝረኸው አሥር አሥር ብር በመላክ አሥር ሰዎችን አታስደስትም?› ትላለች፡፡ እንዲህ ሲባባሉ በጥሞና ሲከታተል የነበረው ፓይለት ደግሞ መስኮቱን ከፈት ያደርግና ‹ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር ሃሳብዎ ቆንጆ ነው፡፡ ነገር ግን አንድ ወይም ሁለት ሰው ወይም አሥር ሰዎችን ከማስደሰት እርስዎ ራስዎ ወደመሬት ተወርውረው 80 ሚሊዮኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሞላ ለምን አያስደስቱም?› በማለት የተለዬ አስታራቂ ሃሳብ ያቀርባል፡፡ ጨቅላ ማለቴ ጠቅላይ ሚንስትሩ ይወርወር አይወርወር ቲቪ ስለሌለኝ እስካሁን አላወቅሁም፡፡ ግን ልብ ይስጠው እንጂ ለምን ይወርወርብን? በየጊዜው ሰው እያጣች የመጣች ሀገራችን ለምን የሀዘን ማቅ ትልበስ? የነአብዱል መጂድን፣ የነክፍሌ ወዳጆን፣ የነከንፈን፣ የነአሰፋ ማሞን፣ የነወይዘሮ አለማሽን፣ የነአቦይ ዜናዊን... ሀዘን በቅጡ ሳንወጣ ለምን ትልቅ የሀገር ሀብት ሊያውም ከአውሮፕላን ይፈጥፈጥብን? የምቀኛ ጆሮ ይደፈን፡፡